የካምቦዲያ ህብረተሰብ ህልውናውን ያረጋገጥ የነበረው በሁለት አቅጣጫ ተዋቅሮ ነበር:: የመጀመሪያው ህብረተሰቡ በአገዶሸ የተዋቀረበት የአደረጃጀት ስልት ሲሆን፤ በእኩልነትና ራሳቸውን ችለው በመንደሮች በሚኖሩ የቤተሰብ ስብሰቦች አንጻር የሚገለጽ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ከታች ወደላይ/ከላይ ወደታች የተዋቀረበት የአደረጃጀት ስልት ሲሆንይህ ደግሞ በእዝ ሰንሰለት አማካኝነት በፖለቲካና፤ በአስተዳደር መስክ የሚታይ አደረጃጀት ስልት ነበር:: ይህ አወቃቀር ከንጉሣዊው አገዛዝ ጋር በጥብቅ የተያያዘ አወቃቀር ሲሆን "ክሜር ሩዥ" የተከሉት መሪዎች ሥልጣናቸውን ለማደላደል በዚህ ዓይነቱ አወቃቀር ለመጠቀም ሞክረዋል::

ቀውስ በሌለበት ጊዜ እነዚህ ሁለት የአወቃቀር ስልቶች በትክክል ስለሚሠሩ ህብረተሰቡ ሚዛናዊ የሆነ አስተዳደር ይኖረዋል:: ቀውስ ሲመጣ ግን አንቅብቃውን እንደ ካንሠር ከቁጥጥር ውጭ የሚያድግበት ከዚህም ጋር ተያይዞ ሌላው የሚከስምበት አደገኛ ሁኔታ ይፈጠራል::

ዛሬ ባለው የቀውስ ሁኔታ ለምሳሌ በአንድ በኩል ህብረተሰቡ ዝግ በሆኑ የቤተዘመድ ስብሰቦች መልክ እየያዘ፤ ጠቅላላው ህብረተሰቡ የጋራ አድርጉ የሚቀበላቸው "ቫሌውስ" እየጠፉ ሲሄዱ በሌላ በኩል ደግሞ ተፍካካሪ የሆኑ የታጠቁ ኃይሎች በያለበት ሲጋው እና ያለን:: ህብረተሰቡ እንደገና እንዲገነባ ከፈለግን ከላይ የተጠቀሰውን ጥንድ የአወቃቀር ዘዴ ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ እንደገና መገንባት ያስፈልጋል::

በአገዶሸ የነበረውን የአወቃቀር ዘዴ ህልውና ለመስጠት የተከታተኑትን የገበሬ ቤተሰቦች እንደገና ማገጣጠም ለዚህም ከገጠር እየፈለሱ ከተማ የገቡትን መልሶ ገጠር እንዲቋቋሙ መርዳት ያስፈልጋል:: በዚሁ ደረጃ ገንዘብ ማውጣት አያስፈልግም:: ምክንያቱም ህብረሰቡ የተመሠረተው ከገንዘብ ውጭ በሚደረጉ ልውውጦች ላይ ነውና::

ከታች ወደላይ፤ ከላይ ወደታች የነበረውም የአወቃቀር ዘዴ እንደገና ከነተሟላ እዝ ሰንሰለቱ መደራጀት አለበት:: ይህንን ለማድረግ ነባር በሆኑ ምልክቶች ወይም "ሲምበል" በሰፊው መጠቀም ያስፈልጋል:: የካምቦዲያን አዲስ ዓመት አከባበር በሰፊው ማጉላት፤ ቤተመንግሥታትንና ገዳሞችን እንደሙዚየም ሳይሆን ለህዝቡ ማስተማሪያ እንደሚሆኑ አድርጉ ማደራጀት... ያስፈልጋል::

ሁለቱን ዘርፎች እንደገና ካዋቀሩ በኋላ በመሃከላቸው ያለውን መቋረጥ እንደገና ለመቀጠልና ለማገናኘት መሞከር ያስፈልጋል:: የህብረተሰቡ መሠረት በሆነው፤ የአገዶሸ አወቃቀርና አገሪቱን በሙሉ በሚወክለው ከታች ወደላይ ከላይ ወደታች አወቃቀር መሃከል በተለያዩ ደረጃዎች የሚሠሩ መዋቅሮች መገንባት ያስፈልጋል:: ከመንደር አንስቶ ቀስ በቀስ ወደላይ ለመውጣትና ሃገር አቀፍ ደረጃ ለመድረስ መማር ያስፈልጋል::

## 4. የስፔን ምሳሌ፣

### በአቶ ጆርዲ ፕላኔስ

የስፔን ህብረተሰብ ለዘመናት መልክ ባለው ሁኔታ ተደራጅቶ የቆየ ህብረተሰብ ነው:: በሶሻል ደረጃ የተዋሀደና አንድነትን የጠበቀ ህብረተሰብ ነበር:: የፖለቲካ አንድነቱ ግን በጄኔራል ፍራንኮ መፈንቅለ መንግሥት ምክንያት ተናጋ:: በተቃዋሚ ኃይሎች አነጋገር ፍራንኮ "ሃገራቸውን ሰረቋቸው" የፍራንኮ ነቀናቂ ራሱን ናሺናሊስት ወይም አገር ወዳድ ብሎ ሲጠራ፣ ተቃዋሚዎቹን ደግሞ ታማኖች/ የሪፐብሊክ/ ወይም "ቀዮች" በሚል ስም ይጠራቸው ነበር:: ከዚህም አለፈው ፍራንኮ ከባህልና ከታሪክ የተወረሱትን የስፔን ብሄራዊ አንድነት ምልክቶች የራሳቸው አርገው ተጠቀሙባቸው::

እንደዚህም በመሆኑ፣ በተለይም እነዚህ ምልክቶች በፍራንኮ የተከከሉ ስለነበሩ በሽግግሩ ዘመን ምን ምልክት ይዘን እንደምንቀሳቀስ ችግር ነበረብን:: ስለሆነም ምልክቶችን በሃሳቦችና በሰዎች ዙሪያ ለመፈለግ ተገደድን::

በመጀሪያ ሃሳቦች ዙሪያ ፈለገን ከተለያዩ ሃሳቦች መሃል ዋና ዋና የመሰሉንን ሶስት ነጥቦች ለመያዝና እነሱን ለማጉላት ወሰንን:: እነሱም፣

1/ ነጻነት ለሁላችንም፣
2/ ጠቅላላ ምህረት ወይም አምነስቲ፣
3/ ለብሄሮች በሙሉ አውቶኖሚ፣

ከዚያ በታዋቂ ሰዎች ዙሪያ ምልክቶች ለመገንባት ሞከርን በዚህ በኩል ከታሉንያ ብዙም ችግር አላጋጠማት:: አርስ በርስ ጦርነቱ ጊዜ የካታሉንያ ራስ ገዝ ሪጅን ፕሬዘዳንት የነበሩትና ጦርነቱ ሲያበቃ በ1939 ዓ.ም. የተሰደዱት ጆሴ ታራዲላስ የሚባሉት አዛውንት ነበሩ:: በስደት በቆዩበት 40 ዓመታት በሙሉ "በስደት ያለው የካታሉንያ ካውንስል" ፕሬዘዳንት ነበሩ:: በዚህ ዘመን ሁሉ የነጻይቱ ካታሉንያ ህያው ምልክት ሆነው ቆዩ:: በሽግግሩ ጊዜ የነበሩት ጠ/ሚኒስትር ይሽንን ሀቅ በመረዳት ጆሴ ታራዲላስ ተመልሰው የፕሬዘዳንትነት በታቸውን እንዲይዙ ፈቀዱ:: በስደት የነበረው ካውንስል ፕሬዚዳንት የአዲሱ አውቶኖመስ ሪጅን ፕሬዘዳንት ሆኑ::

በባስክ አገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አልነበረም:: በዚህ በኩል የአንድነት ምልክት ሆና ያገለገለው ቋንቋና ባህል ነው:: ምንም እንኳን የካስቲሎች ባህል በዙውን ጊዜ እንደ ስፔን ባህል ተድርጉ ቢቆርበም ካታሎኖች፣ ባስኮችና የጋሊሲያ ህዘቦች የራሳቸው የተለየ ባህል አላቸው:: ከዚህም በመነሳት እነዚህ ብሄሮች በቋንቋቸውና በባህላቸው ምልክትነት ዙሪያ መሰባሰብ ችለዋል::

በሽግግሩ መጀመሪያ ላይ በጠቅላላው የስፔን ህዝብ ሌላም አሰባሳቢ ምልክት ነበረው:: ይሸውም ዲሞክራሲ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ነበር:: በዚህ ጥያቄ ላይ ህዝቡ የዲሞክራሲ አምልኮት ነበረው ማለት ይቻላል:: ዲሞክራሲ ሲመጣ ለሁሉም ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ገሪም ድንቅ የሆነ ሁኔታ የሚፈጥር ነገር ይመጣል የሚል አስተሳሰብ ሰፍኖ ነበር::

ከዚህ ተነስተን ነው ዛሬ ወደ መሠረታዊው የስፔን አንድነት ምልከት ወደ ሆነው ህገ መንግሥት የደረስነው:: ይህ ህገ መንግሥት በጠቅላላ ስምምነት የጸደቀ ህገ መንግሥት ነው:: የአንዱን ህብረተሰብ ክፍል አሸናፊነት፣ የሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ተሸናፊነት አያንጸባርቅም:: ከሁሉም ወገን የነበሩት ኃይሎች ከነባር አቋማቸው ትንሽ ትንሽ ሰውተው በጋራ የነደፉት ህገ መንግሥት ነው::

ህዝቡ ለአዲሱ ህገ መንግሥት ያለው ፍቅርና አክብሮት ወደ አምልኮት ይጠጋል:: ከ12 ዓመታት ወዲህ ሰው ሁሉ የሚምለውና የሚገዛተው በዚህ ሰነድ ነው:: ንጉሡም እንደዚሁ የአንድነት ምልከት ለመሆን በቅተዋል:: ግን ይኸ የሆነው 1981 ዓ.ም. የተቃጣውን የመንግሥት ግለበጣ ሙከራ በማክሸፍ ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱ በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት አልነበረም::

በዛሬይቱ ስፔን የዚህ የህገ ምንግሥት ጉዳይ የማይገባበት ነገር የለም:: በተራ ቡና ቤት ጨዋታ እንኳን ወዳጆች ሲወያዩ "ይህ አነጋገርህ ጸረ ህገ መንግሥት ነው" ሲባል መስማት የተለመደ ነው:: በሌሎች አገሮች ቡና ቤቶች እንዲህ ዓይነት ውይይት የሚካሄድ አይመስለኝም::

ለመደምደሚያ ያህል በስፔን አገር ማህበራዊ ውህደትና አንድነት ቀደም ሲል ነበር:: የጐደለን የፖለቲካ አንድነት ነበር:: ይኸንን ደግሞ በህገ መንግሥቱ አማካኝነት ለመገንባት ቻለናል::

## 5. የኮሎምቢያ ምሳሌ፣
በአቶ ሉዊ አለበርቶ ሬስትሬፖ

የኮሎምቢያ ታሪክ በሙሉ የግጭቶችና የድርድር፣ የጦርነትና የሰላም ታሪክ ነው:: ሃገሪቱ ከጂኦግራፊ አንጻር በተሳለቀ ተራሮች የተከፋፈለች ስትሆን ህዝቧም እንደዚሁ የተሰበጣጠረ ናቸው:: ነጮች፣ ጥቁሮች፣ ኢንዲያኖችና ክልሶች አሏት:: በእነዚህ ክፍፍሎች ላይ ደግሞ የሶሻልና የኢኮኖሚ ደረጃ ልዩነቶች አሉ:: ይህ ልዩነት ደግሞ ከዘርና ከቀለም ልዩነቶች ጋር በመጠኑም ቢሆን የተያያዘ ሆና እናገኘዋለን::

የሃገሪቱ አንድነት የተገነባው እንደፈረንሳይ አገርና መንግሥት፣ ወይም እንደ ጀርመን አገርና ህዝብ በሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ሳይሆን አገርና ቤተክህነት በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ላይ ሆኖ እናገኘዋለን::

የ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ በሃገሪቱ መሪዎች መሃከል የነበሩት ልዩነቶች ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ ልዩነቶች ነበሩ:: በአንድ በኩል ደግሞ ይኸንን የሚቃወሙ ሊብራሎች በዚህም የተነሳ ቤተክህነት እዚያው በዚያው በአንድ በኩል የሃገር አንድነት ምልከት በሌላ በኩል ደግሞ የልዩነቶች የግጭቶች ምንጭ ነበረች ማለት ይቻላል::

ይህ የአንድነቱ የግጭት ሁኔታ ከ1950 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ እርስ በርስ ጦርነት አመራ:: ጦርነቱ ማብቂያ ላይ ሁለት ቃሳሳቀ ኃይሎች ሥልጣንን ለመካፈል ተስማሙ:: ግን ከዚያ ወዲህ እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች ሆኑ ቤተክህነት በህዝቡ ዘንድ የነበራቸውን ተቀባይነት እያጡ ሄዱ::

